ተደራሽ እንዳይሆን አድርጎታል:: ሰሊጥ አምራች ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሲወስዱ ለቀን ሰራተኞች የጤና አገልግሎት ለመስጠት ቃል የገቡ ቢሆንም ይህንን አገልግሎት የሚያቀርብ ባለሃብት አየለም:: አንዳንድ አርሶ አደሮች መድሃኒት በሽያጭ ለቀን ሰራተኞች የሚያቀርቡ ቢሆንም የእነዚህ መድህኒቶች ዋጋ ፋራማሲ ውስጥ ከሚሸጥበት ዋጋ የላቀ ነው:: አንዳንድ የቀን ሰራተኞችም በራሳቸው የወባ መድሃኒት ይዘው ወደ አካባቢው ይመጣሉ::

## የስራ ቁሳቁሶች አቅርቦት

አርሶአደሮች ለሰሊጥ የግብርና ተግባራት የሚዉሉ የስራ ቁሳቁሶችን ለቀን ሰራተኞች አይቀርቡም:: የቀን ሰራተኞች እንደ መውሊድ የሚባለውን ለአረም ተግባር የሚጠቀሙበትን የእርሻ መሳሪያ በአቅራቢያቸው ካለው ገበያ በራሳቸው ገዝተው ይጠቀማሉ:: አርሶደሮች አስፈላጊ የሆኑ የስራ ቁሳቁሶችን ሊያቀርቡ ይገባል፡፡



## የቀን ሰራተኛ ነዎት? እንግዲያውስ ለጥንቃቄዎ የሚከተሉትን ይመልከቱ

- በቂ ውሃ ይጠጡ! ከቻሉ ንጹህ ውሃ ፈልገው አሊያም የተገኘውን ውሃ በውሃ አጋር በማከም በቂ ውሃ ይጠጡ::
- ለሰሊጥ ስራ ሲመጡ መድሃኒቶች በተለይ የወባ መከላከያ መድሃኒት ይዘው ይምጡ::
- የሰውነትዎ በሽታን የመካለከል አቅም እንዳይዳከም ተመጣጣኝ ምግብ ይመገቡ:: ከገቢዎ ላይ የተመጣጠነ ምግብ ለመብላት የሚያስችሎን ያክል ይመድቡ:: ገሰርተው የሚያገኙትን ገንዘብ ለሌላ አላማ ሊያውሉት ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን እርስዎ ጤነኛ ሆነው ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የተሻለ ምግብ በመብላት ጤናዎን ይጠብቁ፡፡
- ወደ ተለያዩ የሰሊጥ ማሳዎች ሲጓዙ በግልዎ ከሚሄዱ ይልቅ በቡድን ቢጓዙ ይመረጣል::
- በሚተኙበት ሰዓት ዝናብ እንዳይመታዎት እና በአደገኛ እንስሳት (ነፍሳት) እንዳይጠቁ ሊከላከልሎት የሚችል ልብስ ይዘው ይንቀሳሰሱ::
- ከሌሎች የቀን ሰራተኞች ጋር በመተባበር ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ይጣሩ::

---

### ለበለጠ መረጃ

ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር ዞን ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያዎችን ያናግሩ
ስልክ፡



# በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሊጥ መረብ የሙያ ደህንነትን ለመጠበቅና የጤና ጠንቅን ለመከላከል ለቀን ሰራተኞችና ለአሰሪዎች ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጀ

## መግቢያ

የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ሰሊጥ አብቃይ ቆላማ ወረዳዎች በርካታ የቀን ሰራተኞችን ያስተናግዳሉ፡ በተለይ ሰሊጥ በሚመረትበት የክረምት ወቅት ከ500,000 በላይ የቀን ሰራተኞች ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እርሻ ማረስ፣ ማረም፣ ማጨድ፣ማራገፍ፣ መጫንና ማውረድ የመሳሰሉ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ይሰራሉ። የቀን ሰራተኞች በሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ ውስጥ አይነተኛ ሚና ያላቸው ባለድርሻ አካል ቢሆኑም ለሰሊጥ ንዑስ ዘርፍ እያበረከቱት ያሉት አስተዋጽኦ በብዙ አካላት እየታየላቸው አይደለም። በዚህ በራሪ ወረቀት በሰሊጥ አብቃይ ወረዳዎች የሚሰሩ የቀን ሰራተኞች የስራ እና የኑሮ ሁኔታን መሰረት ያደረገ መረጃ በማቅረብ የቀን ሰራተኞችን እና የአሰሪዎችን ግንዛቤ ለመፍጠር/ለማዳበር እንሞክራለን። በተለይ በኢንቨስትመንት ስምምነት ሰነዱ ላይ ባለሃብት አርሶአደሮች ለቀን ሰራተኞ ለማቅረብ ውል የገቡትን የአገልግሎት ዓይነት እና እየቀረበ ያለውን አገልግሎት እንዲሁም መሻሻል ስለሚገባቸው ጉዳዮች መረጃ እናቀርባለን።

ጽሁፉ በተለይ ለአካባቢው አዲስ የሆኑና ከሌሎች የደጋ ወረዳዎች ለሚመጡ አዳዲስ የቀን ሰራተኞች ስለአካባቢው እና ስለስራ ሁኔታው የተወሰነ መረጃ ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የስራ ሁኔታ ስንል አንድ የቀን ሰራተኛ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሊያጋጥመው የሚችለው አደጋ ወይም የስራ ደህንነት ደረጃ፣ ስራውን የሚያከናውንበት ቁሳቁሶች መኖራቸው፣ መሰረታዊ አገልግሎቶች መሟላታቸው፣ የአካባቢው ሁኔታ እና ሌሎችንም ያካትታል።

## የሙያ ደህንነትን መጠበቅ፣ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ነገሮችን መከላከል

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 92 አንድ አሠሪ ሊያሟላቸው ከሚገቡ ግዴታዎች መካከል፤

- ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤንነት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ ስለሚያስፈልገው ጥንቃቄ ተገቢውን ስልጠና ይሠጣል፤መመሪያ የተሠጣቸው መሆኑንም ያረጋግጣል፤በተጨማሪም የአደጋ ተከላካይ ሠራተኛ ይመድባል፤
- ለሠራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳርያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶች ያቀርባል ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ ይሠጣል ፤
- የድርጅቱ የሥራ ቦታና ግቢ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፤ የሚሉ የአሠሪ ግዴታዎች ይገኙበታል።

ከዚህ በተጨማሪ በኢንቨስትመንት ውል መሰረት ለሠራተኛ ከሥራ አደጋ የተጠበቀ ምቹ የስራ አካባቢ ለመፍጠር ሊዘጋጅ ከሚገቡ ነገሮች መካከል የሚከተሉት መሰረታዊ አገልግሎቶች የገኙበታል።

## የምግብ እና ውሃ አቅርቦት

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በርካታ ባለሃብ አርሶአደሮች ለሠራተኞች የሚያቀርቡት ምግብ የማሽላ ዱቄትና ሽሮ ብቻ ነው። የሚቀርበውም ዱቄት በጥንቃቄ የተያዘ እና ጤንነቱ የተጠበቀ አይደለም። በቂና ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያቀርቡ ባለሃብቶች ቁጥርም ውስን ነው። እንደሚታወቀው የሠራተኞች አመጋገብ ጥሩ ካልሆነ፣ ጤንነታቸው በአግባቡ ካልተጠበቀ፣ ሊታመሙ ይችላሉ። አሰሪዎች በዚህ ምክንይት ምርታቸው ሳይሰበሰብ ሊባክንና ኪሳራ



ላይ ሊደርስ እንደሚችል ግንዘቤ ሊወሰዱ ይገባል። ስለዚህ አርሶአደሮች ለቀን ሰራተኞች የተሸሻለ ምግብና ንጹህና የታከመ ውሃ ሊያቀሩቡላቸው ይገባል።

## የመጠለያ አገልግሎት

በአብዛኛው በካምፕ አካባቢ ካልሆነ በስተቀር ለወቅታዊ ሠራተኞች የመጠለያ ዝግጅት የለም። በሁሉም የእርሻ ጣብያዎች የመጠለያ ዝግጅት ሊኖር ይገባል።

## የመጸዳጃ ዝግጅት

በሰሊጥ እርሻ ወቅት የሚሠማራው የሠው ኃይል በርካታ ከመሆኑ የተነሳ ለተለያዩ በሽታዎች የመጠቃት እድሉ ከፍተኛ ነው። በተለይ አብዛኛው ሠራተኛ ሜዳ ላይ ስለሚጸዳዳ እንደ አተት ለመሳሳሎ ተላላፊ በሽታዎች ሊጋለጥ ይታያል። ባለሃብት አርሶ አደሮች በቂ የመጸዳጃ አገልግሎት ሊየዘጋጁ ይገባል።

## የጤና አገልግሎት

የሰሊጥ ግብርና በሚከናወንባቸው ቀበሌዎች በአቅራቢያ የሚገኝ ሆስፒታል፣ ክሊኒክ፣ ፋርማሲ ወይም ሌሎች የጤና ተቋማት አገልግሎት በጣም ውስን ነው። ራቅ ብለው የሚገኙ የጤና ተቋማትን አገልግሎት ለማግኘት በአካባቢው ያለው የመሰረተ ልማት ችግር በበቂ ደረጃ